# "ኧረ እየተስተዋለ!!...."

## *ወልደሚካኤል መሸሻ - ኔዘርላንድስ*

እየሰማሁ ዝም ማለቱ አላስችል አለኝ። የዛሬውን ሳናይ በትናንቱ መነጽር ብቻ እያየን ማውገዝ ሲቀናን ማስተዋል ከጀመርሁ ሰንበትበት አለ። ብሎም ቀጠለ። ትናንት ያልነውን የተመኘነውን ዛሬ እየረሳን የተቸገርን መሰለኝ። ይህንኑም አስተዋልሁ። እናም በዚህች ምድር ላይ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ከባዱና ገኸርው ሰው መሆኑ ይታወቃል። የሰው ልጅ በአርቆ አስተዋይነቱ ነው ዓለምን እየተቆጣጠረ ያለው። ይህም የአስተሳሰብ ለውጡን አመላካች ነው። ዛሬ መልካም አስተሳሰብ የነበረው ሰው ነገ ወደ ክፉነት ሲለወጥ፣ ዛሬ ክፉ የነበረ ሰው ወደ መልካም ጎዳና ሲሸጋገር፣ ደግሞም አንዳንዱ ከያዘው እርኩስ አስተሳሰቡ እስከወዲያኛው ላይለውጥ ምሎ የተገዘተ ያለ በሚመስል መልኩ መኖሩን ካልታወርን በስተቀር እያየነው ነው። ግን ሰፋ አድርገን ስናይ፣ በየትኛውም መንገድ ቢሆንም፣ የአስተሳሰብ ለውጡ አለ ማለት የሚቻል ይመስለኛል። ይህንኑ የአስተሳሰብ ለውጥ መኖሩን እርግጠኞች ላንሆን አንዳንዶቻችን የማልን መሰለኝ። እንዲህ ለማለትም ያስቻለኝ፣ የሰሞኑ በሥዬና በዶ/ር ነጋሶ ላይ የሚደረገውን እሰጣጋባ ነው። ታዲያም ኧረ እንዴት ነው ነገሩ? አስባለኝ። በዚህ በውጥን አሳቤ ዙሪያም ለግንዛቤ ያህል ሎጅካዊ ምሳሌዎችን ቀንጨብ፣ ቀንጨብ ደግሞ ወደ ሌላውም ጎራ፣ ጎራ እያልኩ ኧረ እየተስተዋለ ለማለት ወደድሁ።

ከሁሉ አስቀድሜ ግን ለአንባቢያን አንዳንድ መንደርደሪያ ጥያቄዎችን ላቅርብ። እስቲ ከመካከላችን ሊንሰን ማንዴላን የማናደንቅ ስንቶቻችን ነን? የምናደንቀውስ ለምንድነው? መለስንና አስተዳደሩን ለምንድነው የምንጠላውና የምናወግዘው? ማንዴላ!፣ ማንዴላ! ስንለው የነበረውን ልደቱን ክህደቱ ብለን የምናብጠለጥለው ለምንድነው? አሁን በቅርቡ ደግሞ በከፍተኛ ደርጃና ስሜት እንጅነር ኃይሉን እያወገዝን ያለነው ለምንድነው? የጠላትን ጎራ እያዳከሙ የራስን ወገን እንዴት መገንባትና ማጠናከር ይቻላል? የመሳሰሉት።

ለሰው ልጅ ክብርና ምንነት ላይ ደንታ ከሌላቸው በስተቀር፣ የሁሉም አገር ሰው በተለይም ኢትዮጵያዊያን ማንዴላን እናደንቃለን ብዬ አስባለሁ። ማንዴላን እኛ ኢትዮጵያዊያን የምናደንቀው፣ አንዳች ነገር ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ሰርቶ ሳይሆን፣ እነዚያ የግፍ ግፍ በአገሩ ሕዝብና በራሱ ላይ ለሰሩት ነጭ ዘረኞች ይቅርታ አድርጎላቸው ቂም በቀልን ለማስወግድ በመቻሉ። በዚህም ስለጥንካሬ፣ ስለሰላም ምንነት፣ ስለርኅራኄነት ለዓለም ሕዝብ ምሳሌ ስለሆነ መሰለኝ። የምንፈልገውን፣ የምንመኘውን ስለፈጸመም ነው መሰለኝ። በዚህም አገሩን ሊከተል ከሚችለው የበቀል ቀውስ በማዳኑ መሰለኝ። ይህም የአስተዋይ ሰው፣ የበሳል ፖለቲከኛ ሰው ተግባር ሆኖ በመገኘቱ መሰለኝ። ይህንኑ የማንዴላን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ በጎ የመሪ ተግባርና አስተሳሰብ ይዘን ነው ጠንካራ ፖለቲከኞቻችን ናቸው ያልናቸውን፣ ለሰው ልጅ መልካም አመለካከትና አስተሳሰብ አላቸው ብለን የገመትናቸውንበማንዴላ እያስመሰልን የምንጠራቸው።

ታዲያም እንዲህ፣ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣ አንዳንዴ ጊዜ ወደ ታሪካችን ዞር ብዬ ማሰብና ማስታወስ እጀምራለሁ። የዚያ የቆፍጣናው የበላይ እርግማንና ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ትግል እሳቱን ለኩሶ በጀግንነት ያለፈው የዚያ የመንግሥቱ ንዋይ የቅጣት ውሳኔ አሳብ ድስኩር ትዝ ይለኛል። እንደዚያ በታቦት ለምነውና አስለምነው አምጥተውት ለስቅላት ሲያዳርጉት የሕዝቡን ሁኔታ የገመተው በላይ፣ <u>"አንች አገሬ ወንድ አይብቀልብሽ"</u> ብሎ ማለፋ ከታሪክ አንብበናል። ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ በወቅቱ ከማንም በላይ በድሎት የሚኖር ቢሆንም፣ ሕዝቡ በዘመነ ንጉሡ የሚደርስበት ሰቆቃ አላስችል ብሎት በመነሳት ያንን ይደፈራል ተብሎ የማይታሰበውን አልጋ አነቃንቅውና ዳግም እንዳይረጋም አደረገው። ከሁሉም በላይ በፍ/ቤቱ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የቅጣት ውሳኔ አሳብ ሲጠየቅ፣ እኔ ሞትን አልፈራም፤ ፍረዱብኝ። ግን የሚቆጨኝ ዓላማዬን ከግብ ያለማድረሴ ነው ብሎ ተነግሮ፣ ለወቅቱ ዳኞችም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ያለፈበት ትውስ ይለኛል።

እምዬ አገራችን መቼም ብትሆን የሚሞትላትን አታጣምና በተመሳሳይ ሌላ አንበሳ ጀኔራል ብቅ ብሎም ዳግም አየን። ጀኔራል ተፈራ ከጓደኞቹ ጋር። ያንን የመንግሥቱን መሳይ ንግግርም አደረገ ለቅጣት ውሳኔ አሳብ። እምዬ ልጆች አሏት፣ ይኖራታልም አስባለኝ። በማንኛውም መንገድ አምባገነኑን የወያኔን መንግሥት እፋለማለሁ ብሎ ከጓደኞቹ ጋር የተነሣው ዶ/ር ብርሃኑ፣ በንብረቱ ጭምር እንደተፈረደበት ሲሰማ፣ ምንም ይወሰድብኝ እንጂ ከምንም በላይ ነጻነቴ ብሎ በፈረጠመ ወኔ መናገሩን ስሰማ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ በወያኔ የግፍ ርምጃ በእሥር ስለሚንገላተቱት የ80 ዓመቱ ሽማግሌ አባቱ ሲጠየቅ፣ አባቴ ላይ የደረሰው በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከደረሰውና እየደረሰ ካለው የተለየ አይደለም። አባቴ ከሕዝብና ከአገር በላይ አይደለም ያለውን ሳይና ስሰማ፣ ቢሆንም ወንዶች አሁንም እምዬ አሏት አሰኘኝ። እንደነ ውዷ ብርቱካን የመሳሰሉት ኢትዮጵያዊነትን፣ አንድነትን፣ ሰላም ብልጽግናን፣ ለሕግ በላይነት ከሞት በቀር ምንም አይነቀንቀኝም፣ ለማንም አልበገርም፣ አላጎበድድም ብለው የተነሱትን ሳይና ስሰማ፣ ኧረ አገሬ ከወንድም ጀግና ሴቶች አሏት እልና እጽናናለሁ። እምዬ የወላድ መካን አይደለችም፣ አትሆንምም እላለሁ።

<u>"በእኔ እምነት ይሄ ሁሉ ከሕግ የወጣ ዛቻና ማስፈራሪያ እየደረሰብኝ ያለው ስለቃላት ጨዋታ ወይም ስለተዛባ እውነት ወይም ስለተጣሰ ሕግ አይመስለኝም። መልእክቱ ግልጽ ነው። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰላማዊ ታጋዮች፣ በሰላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ የሚቻለው በሕገ-መንግሥቱ በተሰመረው መስመር ሳይሆን፣ ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ ነው</u>

የሚል ነው። ይህ ደግሞ እሺ ወይንም አዎ ማለት ለእኔ እጅግ ከባድ ነው።”

ታላቋ ታጋይ ዳግማዊት ጣይቱ ወይም ቴዎድሮሳችን ብርቱካን ሚደቅሳ ዳግም ታፍሳ ወደ ተለመደው ዘብጥያ ከመውረዷ በፊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያኖረችው የኑዛዜ ቃል፣ የኢትዮጵያዊነት ተምሳል ቃል፣ የአንድነት ቃል፣ የአይበገሬነት ቃል፣ የትግል አቅጣጫ አመላካች ቃል። ብርቱካን በዚያ ጽሁፏ የዘረዘረቻቸውን አጠቃልላ በዚህ ትምህርት-ጥቅስ ውስጥ ባለው መልክ ሸክን፣ እጥር፣ ምጥን አድርጋ አስቀምጠዋለች። ከቆራጥ ሰው አንደበት የሚወጣ እውነተኛ ቃል። ሁሌ ከኢትዮጵያዊያን አእምሮ የማይጠፋ ቃል። ሁሌ ተስፋ የሚሰጥ፣ ብርታት የሚሰጥ ቃል።

የለም፣ አሻፈረኝ እምቢ ለማህተቤ፣ ለአገሬ ለወገን፣ እውነትን እንጂ ሐሰትን ላልሰንቅ፣ ላልከተል፣ ላላስተምር ቃል ገብቻለሁ። ቃሌ ቃል ነው። አቋሜ የማይናወጥ አቋም ነው። ለትውልድ የማወርሰው፣ ያለአባት፣ ያለ እናት እንድታድግ ለዳረግኋት ለአንድዬ ልጄ የማወርሰው እውነት እንጂ፣ ዲሞክራሲ የሰፈነባት አገር እንጂ፣ ሕዝቦችዋ እኩል የሚታዩባት አገር እንጂ፣ የሕግ በላይነት የተከበረባት አገር እንጂ አምባገነንነት የሰፈነባት፣ የተከፋፈለች አገር፣ ሐሰት የነገሰባት አገር እንዳይሆን ምያለሁ ብላ ያለኃጢአቷ፣ ያለወንጀሏ ያውም ሴትነቷ ሳይበግራት፣ እንደ ነፍሰገዳይ በአንድ እጅግ ጠባብና ጨለማ በሆነ ክፍል ቤት ታፍና፣ ተለጉማ ጊዜዋን እየቆጠረች ያለች ብርቱካን።

ብርቱካን የምትወዳትና ከአብራኳ የተገኘችውን ጨቅላ ሕጻን ልጇን በኘያ እድሜያቸው በማይችለው እናቷ ላይ ጥላ ነው ከሕግ በላይ ምንም የለም፤ ለዚህም እሰዋለታለሁ፤ እስከሚከበር ድረስ ለማንም እጄን አልሰጥም፣ ለልጄና ለትውልድ የማወርሰው ይህንኑ ነው ብላ፣ ፊቴንም አላዞርም ብላ፣ የሚመጣባትን ሁሉ እሸከማለሁ አሻፈረኝ ብላ ዳግም ለዘብጥያ የተዳረገችው። ወያኔ የፈለገውን ቢያደርግባት፣ የፈለገውን ቢፈጽምባት ለአንድነት፣ ለሰላም፣ ለዲሞክራሲ ባላት የማይናወጥ አቋሟ እንደምትገፋ በገባችው ቃል ጸናች።

እናም፣ ብርቱካን እነ ዶ/ር ብርሃኑ ከእንግዲህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ ትግል ብቻ ለውጥ አይመጣም ብለው ሁለገብ ትግል መርጠው ራሳቸውን ከቅንጅት ፓርቲ አባልነት ባገለሉ ወቅት፣ በአንድ ጽሑፏ እንደመቃወም ብላ እንደነበር ትዝ ይለናል። የሚሰራ ሰው ይሳሳታል። ዋናውና ቁም ነገሩ አይቶና መዝኖ ራስን ማረሙ ላይ ነው። ብርቱካን በዚያን ወቅት እንደዚያ ብትልም፣ የኋላ ኋላ እስከአንድነት ፓርቲ ማቋቋም አድማስና ከዚያም ባሻገር እውነት በተናገረች እየተፈጸመባት ካለው ጋር አያይዛ፣ በሰላማዊ ትግል አካሄድ ላይ እየቀጠለ ያለውን የመንግሥት ደባ አይታና ተገንዝባ ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጸችውን የምስክርነት ማረጋገጫ ኑዛዜ ሰጥታለች። ከድርጊት ጋር የተመዛዘነ፣ ከማስረጃ ጋር የተመዛዘነ የእውነተኛ ዳኛ ፍርድ። ዳግም ዳኝነት፤ ዳግም ፍትህ።

በዚያ ሰሞን ይህ እኩይና መሰሪ መንግሥት ደግሞ ቸገረውና በእናቷ በኩል ብቅ ሊልባት ሞከረ። እኔ ደካማነኝ፣ መንግሥት መሐሪ ነውና አንድ ጊዜ ቢፈታልኝ የትም አላነቃንቃትም አስባለ በአንድ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ። የእናት አንጀት ሆነና። የእድሜያቸውን መግፋትና መድከም ምክንያት በማድረግ እንዲፈቷት ልመና እንዲያቀርቡ ዓይነት አካሄድ። ብርቱካን ግን ብርቱካን ነች። ከብረት የጠነከረች፣ ከዕንቁ የከበረች። እርሷ እንደሆነች ምድር ከፍ ቢል፣ ሰማይ ዝቅ ቢል እንኳን እጅ መስጠት አይቻላትም። አቋሟ በሰብአዊ መብት ላይ ነውና፣ አቋሟ በዲሞክራሲ ማበብ ላይ ነውና፣ አቋሟ ለአንዲት አገር ለኢትዮጵያችን ልዕልና ነውና፣ አቋሟ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት ነውና፣ አቋሟ ለሕግ በላይነት ነውና መትረየስና ቦምብ ተቀናጅተው ቢመጡባት እንኳ ብርቱካን ንቅንቅ ላትል አንዴ ሆናለች። እናም፣ የመለስ መንግሥት በብርቱካን ላይ እንደተለመደው ተራ የማጭበርበር ተግባር ሊፈጽም ከቶውንም እንደማይቻለው ሆነ፡፡ ሴቷ አምበሲት፣ ዳግም ጣይቱ፣ ዳግም ቴዎድሮስ። እንግዲህ ብርቱካን ውሸትን ላታስተናግድ ቆርጣ ያለኃጢአቷ ፍዳን ስትቀምስ እያየናት ነው። የታሰረ ሰው ፍጹም ነጻነቱን የተገፈፈ ሰው ነው። በቃ ከሞቱት በላይ፣ ካሉት በታች መሆኑ ነው። የዕድሜ ልክ ሲሆን ደግሞ እስከ ተስፋ መጨለም ይደርሳል። ይህ ግን ከላይ እንዳልሁት እንደብርቱካን ለመሰለ ጀግና ምኑም አይደል። ግና ይህች ወጣት እንዲህ ዓይነት መስዋዕትነት ስትከፍል እኛስ ምን አድርገናል? የት ነን? አሁንም በትናንቱ?

እናም፣ ወገኖቼ አንዱን አንስቼ ሌላ መደረቤ የትናንቱ እይታችን ለዛሬው አስተውሎት ይበጅ ካልሆነ በስተቀር፣ ወሳኝ አይሆንም ሊሆንም አይችልም ለማለት ነው። የትናንቱን ማንዴላችን በዚያ ዓይነት ስናሰናብት፣ ዛሬ ደግሞ ከሕግ በላይ ምንም፣ ማንም የለም። እኔ ለሕግ እንጅ ለምንም አልገዛም አልበገርም ብላ እውነትን ለተናገረች፣ እውነትን ስላወጣች ያለ ሕጋዊ ሥነ-ሥርዓት በእስር የምትማቅቀውን ብርቱካንን ማንዴላ ብለናታል። የለም እንጅ ቢኖር ከዚህ በላይ ባልናትም ነበር። ታዲያ አገባቤ በዚህች ጽሑፌ ስለብርቱካን ብዙም አውርቼ ለማጠቃለል አይደለም። ከተነሳሁበት ጭብጥ ጋር ለማያያዝ ፈልጌ እንጅ። ለመሆኑ እንዲህ ዕንቁ የሆነችዋ ብርቱካን በሕዝብ እይታ እንዴት ገባች? መቼ? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ሰሞኑን እጅግ አድርጌ ከምወዳቸው፣ ከማደንቃቸውና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማያወላውል አቋም ባላቸው ኢትዮጵያን መድረክ ላይ ተነሳው እሰጣገባ ክርክር ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት ያስችላል ብዬ እገምታለሁ።

ሥዬ አብርሃ ቀንደኛ የወያኔ አባል መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ ጎልት አይወራ እንጅ ከጦር ሠራዊቱና ከፖሊስ ሠራዊቱ ቀጥሎ ከፍተኛ በትር ያረፈበት ፍ/ቤት ነው። በወያኔ ቻርተር ወቅት በያለበት በፍ/ቤቶችና በዳኞች ላይ ዘመቻ በሚካሄድበት ጊዜ ሥዬ አብርሃ በምክር ቤቱ ላይ ተነስቶ ፍ/ቤት ምን ያደርግልናል። በቀድሞ አሰራራችን ብንቀጥልበት ነው የሚሻለን በማለት የተናገረውን አስታውሰዋለሁ። በዚህም አነጋገሩ በዳኞች ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳተረፈም ትዝ ይለኛል። ይሁንና በኢትዮጵያ አቆጣጠር በተለይ 1992 ዓ.ም ወይም እ.ኢ.አ 2000-2001 ከኤርትራ ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ በውን ያልጠበቀውን ያየበት ጊዜ ከተፍ አለ፣ የወያኔ

መሰነጣጠቅ የተከሰተበት። በአንደኛው ጎራ በሥዬ መሪነት ሊብራል ዲሞክራሲ አሳብ አራማጆች (የምዕራባዊያን ዓይነት)፣ የአሁኑ አርና ትግራይ አባላት የሆኑት በሙሉ፣ በሌላኛው ጎራ ደግሞ መለስና የአሁኑ አስተዳደር አብዮታዊ ዲሞክራሲ (የማርክስዝም ሌነኒዝም ተቀጽላ) በመሆን። እነ ሥዬ ሁሉን ነገር ያጠናቀቁ መስሏቸው ሲዝናኑ መለስ በለመደው ካራቴ ቀደማቸውና እቅዳቸውን ወዲያውኑ በቁጥጥሩ ሥር አዋለባቸው። ታዲያም መለስ ጠላቴናቸው የሚላቸውን የመከፋፈል ልዩ ጥበቡ ቀንደኛ ነው ብሎ የገመተውን ሥዬን ለይቶ ከእናቱ በስተቀር አንድም ቤተሰብ ሳይስቀር ወደ ዘብጥያ አወረዳቸው። የተለኮሰውንና የተቀጣጠለውን እሳት በዚህ ዐይነት አዳፈነው።

ሥዬም ከቤተሰቡ ጋር ያ ያሳድድ ወደ ነበረበት ፍ/ቤት መቅረቡ አይቀሬ ሆነ። አይ ጊዜ አሰኘኝ በወቅቱ ታዲያ። ጊዮርጊስ የመጀመሪያ ፍ/ቤት ችሎት ለጊዜ ቀጠሮ ሥዬ ሲቀርብ ሕዝቡ ያንን ያለፈውን የሥዬን ተግባር ወደ ኋላ ወርውሮ ሥዬ! ሥዬ! እያለ ማጀቡን ጀመረ። ያ ሰፊ ግቢ ሥዬ በሚቀርብ ዕለት በሰው ብዛት ይጨናነቃል። እንዲህ ያለ ነገር ሲከሰት የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ማቀጣጠሉን ይውቁበታልና አቀጣጠሉት። ሕዝቡን ቀሰቀሱት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት፣ ገራገርነት፣ ርኅሩኅነት፣ እና ይቅርባይነትን ይበልጡን ያየሁትና ያስተዋልሁት ያን ጊዜ ነው። ይህም ለእኔ የበለጠ ርኅራኄ እንዲያድርብኝ፣ በበለጠ ሰብአዊነት፣ የበለጠ ለሰው ልጅ ክብር እንድሰጥ ዝግጁ እንድሆን አደረገኝ። የዚያን ጊዜ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነበርኩኝና ብርቱካንም ከሌላ ችሎት የሥዬን ጉዳይ በሰብሳቢ ዳኝነት እንድትመራ ወደ ችሎቱ መመደቧን፣ ምክንያቱም መንግሥት በሚፈልገው ዓይነት ለሥዬ የዋስትና መብት እንድታሳጣው ዘንድ እምነት ስላሳደረባት መሆኑንም ከአለቆች ሰማሁ። ችሎቱ በወቅቱ ሦስት ዳኞች የሚሰየሙበት ነው። ሥዬን አጃቢ ሕዝብም በየቀጠሮው እየቀረበ፣ ሰብሳቢ ነችና በምትሰጠው ትዕዛዝ እየተማረከና እየተመሰጠ ብርቱካን! ብርቱካን! ማለት ጀመረ። ብርቱካን ቀደም ብላ ዳኝነቱን ሥራ አቋርጣ በ92ቱ ምርጫ በግል ተሳትፋ ስለነበር በመጠኑም ቢሆን በሕዝቡ ዓይን ገብታለችና። በወቅቱ ብርቱካን ወደ ለቀቀችው ሥራ ወደ ዳኝነቱ መመለሱን ወያኔ እንደውለታ ቆጥሮ ይመስለኛል እንደዚያ እምነት ያደረበት።

የፍ/ቤት መሪዎቻችን ታዲያ የሕግ ጠባቂዎች፣ ብሎም የሕግ በላይነትን አስከባሪዎች ሳይሆኑ፣ የአስፈጻሚውን፣ የመንግሥትን ሕልውና በተቻላቸው መጠን አስከባሪዎች በመሆናቸው በብርቱካን ላይ የተቻላቸውን ጫና ለማድረግ በወቅቱ ሞከሩ። በተረዋ በሌሎች ሁለቱ ዳኞች ላይ ጫና አድርጋ እንደመለስ ፍላጎት ታስወስናለች ተብላ እምነት የተጣለባት ቡርቴ፣ ለማለችለት እውቀት፣ ለገባችለት ቃል ተገዥ ሆና፣ ለሌሎች ጥንካሬ ሰጥታ ለሥዬ የዋስትና መብት እንዲጠበቅለት አድርጋ ከጓደኞቿ ጋር በየነች። ከዚህ በኋላ ብርቱካን በፍ/ቤት መሪዎችና በመንግሥት ጥርስ ስትገባ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ሙገሳና ውዳሴ አገኘች። ዳኝነት ከብርቱካን ወዲያም ዓይነት ሆኖ ተቆጠረላት። ብርቱካን ለማንም፣ ለምንም የማትበገር መሆኗን ያስምሰከረችውም በዚህ ወቅት ነው። እናም፣ ከዚህ በኋላ የሥዬ ጉዳይ ሲነሳ ብርቱካንም ከዚያ ከፍርዷ ጋር በሰው አእምሮ ውስጥ ድቅን ማለቷ አይቀሬ ሆነ።

ምናልባትም በሕዝብ ዘንድ ጎልቶ አይውጣ እንጅ፣ የሕዝብን እይታ አይሳብ እንጅ እንደዚህ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የዳኝነት ክህሎታቸውን ያሳዩና የሚያሳዩ ዳኞች ነበሩ፣ አሉምም። በምሳሌነት ከዚህ በፊት ለመጥቀስ እንደሞከርሁት የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረው የእንዳለ ተሰማ የሐቤስ ኮርፐስ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ብይን። የደርግ ባለሥልጣኖች እየታደኑ በሚያዙበት ወቅት እንዳለ ተሰማ ወደ ፍ/ቤት በሐቤስ ኮርፐስ ጥያቄ ቀርቦ፣ ልዩ ዐቃቤ ሕግ እንዳለን የያዘበትን ምክንያት በበቂ ሳያስረዳ በመቅረቱ፣ የችሎቱ ዳኞች በነጻ ይለቁታል። እንዳለ ተሰማም እንደሥየ ተይዞ የተመለሰው ከከፍተኛ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ሳይወጣ ነው። በወቅቱ እነዚያ የችሎቱ ዳኞች ብቻ አልነበሩም በአስተዳደሩና በመንግሥት ጥርስ የገቡት፣ መላው የዳኝነቱ አካል ጭምር እንጅ። ከዚህ በኋላ ነው መንግሥት ፍ/ቤቱን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ዘመቻ ማጧጧፍ የጀመረው ለማለት ይቻላል። ታዲያ እንዲህ ከሆነስ፣ እንደዚያ የብርቱካን ስም ለምን በሥዬ ጉዳይ ገኖ ሊወጣ ቻለ የሚል ጥያቄ አእምሯችን ያጭር ይሆናል።

ሁልጊዜ ሥራዎች፣ እውነቶች እነደየመልካቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለያያሉ። ከፍ ሲል እንዳልሁት ከጥቂቱ በስተቀር ማለት ይቻላል የወያኔን አስተዳደር ሕዝቡ መጥላት የጀመረው ከጊዜ በኋላ ሳይሆን፣ ገና ከጧቱ ነው። እንደዚያ ጠንካራና አኩሪ ሠራዊትን ከማፍረሱ ጀምሮ፣ በዘር ፖለቲካው ተከባብሮ ይኖር የነበረውን ሕዝብ በጎሳ፣ በሃይማኖት ቁም ስቅሉን ማሳየቱ፣ ኧረ ስንቱ? ይህ ሁሉ በአንድ በኩል ሲደማመር፣ በሌላ በኩል የአማራውን ብሔረሰብ ለማዳን ሲሉ በከፍተኛ ወኔ ከተነሱት ከፕሮፌሰር አሥራት በስተቀር በወቅቱ ይህን ያህል ወያኔን ይቋቋማል ተብሎ በማይገመትበት ወቅት ከዚሁ ከግዙፉ ሰይጣን አካል በመሪነት ሥዬ ብቅ አለ። እርሱና ተከታዮቹ የሊብራል ዲሞክራሲ ለማራመድ ታጥቀው መነሳታቸውን በየግል ጋዜጦች ማወጅ ጀመሩ። በወቅቱ የሕዝቡ ቡና መጠጫም ይኸው ሆነ። እሠይ ወንድ ነው። ለካስ ሁሉም ወያኔዎች አንድ አይደሉም። ጊዜ የሚጠብቁ ነበሩ ማለት ነው እያለ። በቃ የሥዬ መልካም ስም ተመለሰ ዓይነት ሆነ። እኔ ታዲያ በወቅቱ ትዝ ያለኝ የጎርባቾቭ ክስተት ነበር። ጎርባቾቭ በግዙፉ የቀድሞው ሶቭየት ሕብረት ፓርቲ በቦልሸቪክስ ውስጥ ተወልዶ፣ ለሥልጣን የመብቃቱን ዕድል እንዳገኘ ጊዜም ሳይወስድ ፕሮስትራይካ በሚል ተሐድሶ በኮምኒዝም እስር ውስጥ የነበሩት ሁሉ ወደ ነጻነት ጎዳን እንዲወጡ በር የቀደደ መሆኑን ይታወቃል። በዚህም በዓለም ተደናቂ መሪዎች አንዱ ሆኖ ለኖቬል ተሸላሚነት የበቃ ነው። እናም፣ በወቅቱ ለካስ ነገሩ ከሊጥ ጋር የተገኘ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ሆነና ነው እንጅ፣ በመጥፎቹ ውስጥ ጥሩዎቹም አሉ፤ ይኖራሉም የሚል ጽኑ እምነት አደረብኝ።

ከጀመርሁ ላይቀር ሌላም ልጨምር ስለሥዬ ጉዳይ ፊት ለፊት ከአንደበቱ የሰማሁትን። በነብርቱካን ትእዛዝ በአንድ ምሽት ለኮራፕሽን እስረኞች በሙሉ ዋስትና የሚያስከለክል ሕግ እንደወጣ ጉዳዩ የዞረው ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ነበር። የጊዜ ቀጠሮ እንደገና ተጀመረ በጠቅላይ ፍ/ቤት። በወቅቱ ታምራት ላይኔም ለሁለተኛ ግዜ ከሥዬ ጋር ተከሶ ቀርቦአል። አባተ ኪሾ የደቡብ ሕዝቦች ፕሬዚዳንት የነበረው፣ ቢተው የሚባል የወያኔ አባል በሥዬ

ደጋፊነታቸው ኮራፕትድ ናቸው ተብለው ቀርበዋል። ለነገሩ እኔ ሥዬ በወቅቱ ሁሉንም የክልል ፕሬዚዳንቶችን አሰልፈው እንደነበር ነው። የአሁኑ የአዲስ አበባ ከንቲባ ተብየው ኩማ ደመቅሳ፣ በወቅቱ የኦሮምያ ፕሬዝዳንት የነበረው፣ አይሸሹም ያረጋል የቤኒሻንጉል ፕሬዚዳንት የሆነው የመለስን እግር ስመው ይቅርታ ጠይቀው ምህረት እንዳገኙ ሰምቻለሁ። እናም ለነሥዬ ጉዳይ አምስት ዳኞች የተሰየምን ሲሆን፣ አንዱ ነበርሁ በወቅቱ። የጊዜ ቀጠሮ መግለጫ እና ጥያቄው ከጸረ-ሙስና ኮሚሽን ቀርቦ ለተከሳሾች እንደተነበበላቸው፣ የጊዜ ቀጠሮ ለመስጠት ስንል፣ ሥዬ የምናገረው አለኝና ክቡራን ዳኞች ስሙኝ በማለት ጠየቀ። ጉዳዩ የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ ስለሆነ ምንም አንሰማህም አለ ሰብሳቢው። በዕለቱ ሰብሳቢ የነበረው በፍ/ቤት ታሪክ አንጋፋ ዳኛ የነበረ ፍሰሐ ወርቅነህ ነው። ሰብሳቢ እንዲሆን በአቶ ከማል ተመድቦ የነበረው በወቅቱ እስከአሁን ያለው ም/ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መንበረፀሐይ ታደሰ ነው። መንበረ ምደባውን እንደሰማ በሕመም አሳቦ ከፍ/ቤት ይቀራል። ለምን? ወደኋላ እመለስበታለሁ። እናም ኧረ እባካችሁ ያለኝ አንድ መድረክ ይህ ፍ/ቤት ነው እያለ መማጸን ጀመረ። ሰብሳቢው አሻፈረኝ ይላል። ይህን ጊዜ የኛ ጠልቃ መግባት ግዴታ ነበርና ኧረ እንስማው እንጂ ፍሰሐ ብለን ኮምጨጭ ስንልበት ፍሰሐ ፈቀደለት።

ሥዬም ጀመረ። እኔ የፈጸምሁት አንድም ኮራፕሽኝ የለም። ማስረጃም ጠላቶች አያገኙብኝም። እኔ ከመላ ቤተሰቤ ለእሥር የተዳረግሁት፣ ወደ ስህተት ጎዳን ገብተናል፤ ሕዝቡ ጠልቶናል፤ ራሳችንንም ለምን አንፈትሽም? እያልሁ የሕዝቡን ስሜት ከቀሪ ጓደኞቼ ጋር ካየሁና ካስተዋልሁ በኋላ ከመለስ ጋር መጨቃጨቅ ጀመርሁ። በተለይም፣ በተፈጠረው የጦርነቱ ድል አጋጣሚ በስህተት ያስወሰድነውን ወደባችንን ሳናስመልስ ጦርነቱን ማቆም የለብንም ብዬ በጣሙን ተከራከርሁ። ግን ባለው የጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ ጦርነቱ እንዲቆም አደረገ። ከዚያም አልጀርስ ሮጦ በመሄድ ያንን እንደገና እጅ የሚያሰጥ ፊርማ አኑሮ መጣ። ከዚህ በኋላ በመካከላችን የነበረው ያለመግባባት ፍጹም ሊጣጣም አልቻለም። ስህተታችንን ማረም አለብን ማለቴን አጠናከርሁ። ይህ የማርክስዝም ሌኒንዝም አካሄድ አያዋጣንም። አመራራችን በሊብራል ዲሞክራሲ መሠረት ላይ መሆን አለበት ብዬ ከጓደኞቼ ጋር መከራከሬን ቀጠልሁ። እናም መለስ እኔን ለማስወገድ በጠነሰሰው ተንኮል እስከነቤተሰቤ ለእስር አበቃኝ። እውነታው ይህ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቅልኝ በማለት ለተሰጠው ዕድል ምስጋና ሰጥቶ ያሳረገው ንግግር ከቶውንም አይረሳኝም በወቅቱ ከሰማሁት ወሬ ጋር ተዳምሮ። እናም ትዝ ይለኛል። በወቅቱ ፍሰሓ በጭንቀት ውስጥ ገብቶ ለማስቆም እየሞከረ ነበር ከኋላ ከአለቆቻችን ሊደርስበት የሚችለውን እያሰበ። ነገር ግን ተው እባክህን ይጨርስ በማለት በዳኝነት የሽኩትኩታ አነጋገር እስከ መጨረሻው አስዘለቅነው። በዕለቱ ከሥዬ ቀጥሎ ታምራትም ዕድል እንዲሰጠው ጠይቆ ፕሬዚዳንት ኢሳያስን ጭምር የተናገረው አለ። የርሱን በሚመለከት ወደፊት በሌላ ጽሑፌ እመለስበታለሁ።

በዚያን ሰሞን ስለስዬ ምዝበራ ብዙ መንግሥት አውርቶና አስወርቶ ስለነበር፣ እኔ ምንም ኮራፕሽን አልፈጸምሁም፤ ማስረጃም አያገኙብኝም የሚለውን የሥዬን አነጋገር እስቲ ይሁና ከማለት በስተቀር ማመን ያስቸግር ነበር። እናም፣ በመጀመሪያ ቀጠሮ የተለመደውን ሙሉውን የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ሰጠን። በቀጣዩ ዐቃቤ ሕጉ አላጠናቀቅሁም ተጨማሪ ሙሉው ይሰጠን ብሎ ጠየቀ። እኛ ግን ለ10 ቀን ብቻ ሰጠን። ጸረ-ሙስናና ዐቃቤ ሕጉ መደናገጥ ያዙ። እነርሱ ሁሉን ነገር ከመጀመሪያው እንደጀመሩ ዓይነት ሲቆጥሩ፣ እኛ ግን በሥር እነብርቱካን ዘንድ የተደረገውን በሕሊናችን እያሰብን ነበር። አካሄዳችን ያላማረው ዐቃቤ ሕግ ለሦስተኛው ቀን ቀጠሮው ከመግባታችን በፊት እጽ/ቤታችን አስፈቅዶ ገብቶ፣ እባካችሁ ሥዬ ላይ ማስረጃ ለማግኘት በጣም ተቸግረናል። አሁን ታምራት ላይኔ የምስክርነት ቃሉን እንደሚሰጥበት ቃል ገብቶልናልና ረዘም ያለ ቀጠሮ እንዲሰጠን እለምናለሁ ብሎ እንደማሳሰብ ዓይነት ጥያቄ አቀረበ። ነገሩ አበሳጨንና አንዳንዶቻችን ዐቃቤ ሕጉን እንደማባረር ዓይነት አድርገነው ወጣ። ግን ተመካከርን። እውነትም ይህ ሰው እንዳለው እነዚህ ሰዎች፣ በዚህ ሰው ላይ ማስረጃ የላቸውም ማለት ነው? ታምራት ወደዚህ ክስ የገባው በርግጥ ከሥዬ ጋር ወንጀል ሰርቶ ነው ወይስ ያለበትን ቁስል ምክንያት በማድረግ አስገድደው ምስክር ለማድረግ? (የ17 አመት ፍርደኛ ነውና)። ታምራት ሊመሰክርበት ቃል ከገባ ለምንስ ረዘም ያለ ቀጥሮ ያስፈልጋል? በሚሉትና በመሳሰሉት ነጥቦች ዙሪያ ተወያይተን መደምደሚያ ላይ ደረስን። እናም የ7 ቀን ጊዜ ብቻ ከማስጠንቀቂያ ጋር መስጠት እንዳለብን ተስማምተን ወደ ችሎቱ ገባን። እንደተለመደው ዐቃቤ ሕግ ምርመራውን አጠናቅቆ እንደሆነ ጠየቅነው። አልጨረስንም። እንደሚታወቀው ሙስና በምስጢር የሚፈጸም በመሆኑ ውስብስብ ነው። ብዙ ጊዜ ያስፈልጋል። እናም ሌላ ተጨማር የ14 ቀን ቀጠሮ ይሰጠን በማለት ጠየቀ። እኛ ግን በተመከከርነው መሠረት የ7 ቀን ጊዜ ሰጠን። በዚህ ጊዜ ባያጠናቅቅም ክሱን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ፣ አለዚያም ፍ/ቤቱ መዝገቡን የሚዘጋ መሆኑን አስጠንቅቀን።

በመሠረቱ የሙስና ወንጀል ማስረጃዎቹ መታወቅ ያለባቸው አስቀድሞ እንጂ ፍ/ቤት ከቀረበ በኋላ መሆን አልነበረበትም። ምናልባትም የጊዜ ቀጠሮና የፍ/ቤት አስፈላጊነቱ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ብቻ ነው። ታዲያ በሥዬ ላይ እየተደረገ የነበረው ስናይ፣ ወንጀሉ የተነገረው ሳይሆን፣ በሕዝቡ ዘንድ እንደሚወራው ራሱም እንዳለው፣ የፖለቲካ ጉዳይ ነው የሚያስብል ሆኖ ነው የተገኘው። ያ የ7ኛው ቀን ከተፍ አለ። እነደነገ ችሎት ልንገባ ዛሬ መነበረፀሐይ እቢሮው አስጠራኝ። ቡና እንደምወድ መንበረ ስለሚያውቅ ጸሐፊውን ቶሎ ለወልዴ ቡና አላትና ለብርቱ ነገር ፈልጌህ ነው ብሎኝ እንድቀመጥ ጠይቆኝ ተቀመጥሁ። ምንድነው? ብዬ ጠየቅሁ። ለምንድነው በሥዬ ላይ የተቻኮላችሁበት? መንግሥት እኮ ሕጉ አሻሽሎ ወደ እኛ ሲልክ፣ ከእኛ የሚጠብቀው ነገር አለ። በዚህ አካሄዳችሁ ፍ/ቤቱን ልትገድሉት ነው። ደግሞ አንተ ለምንድነው እንደዚህ የምትሆነው? ጉዳዩ አስቸጋሪ እንደሆነ ታውቀዋለህ። ዐቃቤ ሕግ ብዙ ጊዜ ያስፈልገዋል። ስለዚህም ነገ በሰጣችሁት ማስጠንቀቂያ መሠረት የመጨረሻ እንዳታደርጉ ነው የምጠይቀው አሁን። ዳኞች ስለሚይዳምጡህ አንተ ግፊት ማድረግ አለብህ አለኝ። ያላስብሁትና ያልገመትሁት ስለሆነ ተደናገጥሁ። ግናም በዚያች ቅጽበት ራሴን አረጋግቼ፣ እንደ አቶ መንበረ

የምንሰራው የዳኝነት ሥራ አይደል? የጊዜ ቀጠሮ ምን እንኳ በሕጉ ላይ ወሰን ባይኖረውም፣ ግምቱ ለዳኛው ተሰጥቶአል። በተለይም በእኔ ግምት ለዐቃቤ ሕግ ከሥር ጀመሮ የተሰጠው ጊዜ ከበቂ በላይ ነው። ይህንኑ አውጥተን አውርደን ነው ትዕዛዙን የሰጠነው። እናም፣ እኔ በበኩሌ አሳቤን ልለውጥ አልችልም አልኩት። በቃ ይኸው ነው ወልዴ? ብሎ ጠየቀኝ። አዎን መንበረ ይኸው ነው አልኩት። ተው እንግዲህ እኔ አንተን አላውቅህም ማለት ነው አለኝና ከቢሮው በዚህ ዓይነት ወጣሁ። ልክ ከቢሮው ወጥቼ ከትንሽ ቆይታ ሽንት ቤት ደርሼ ወደ ጽ/ቤቴ ለመግባት እየተንደረደርሁ እያለሁ፣ አብረን ከነበርነው ዳኞች አንዱ የሆነው ዳኜ መላኩ ወደ አቶ መንበረ ቢሮ ሲገባ አየሁ። በቃ ነገ ጉድ ፈላ አልሁ በሆዴ።

ይህንኑ በሆዴ እንደያዝሁ፣ በነጋታው ከሰዓት በኋላ ወደ ችሎቱ ከመግባታችን በፊት ወደ ምንሰበሰብበት ክፍል ገባን። ወደ ክፍሏ መግባታችንን ሲጠባበቅ የነበረው፣ የጸረሙስና ዐቃቤ ሕግ አስፈቅዶ ይገባል። ምንድነው ብሎ ፍሰሐ ይጠይቃል። ዐቃቤ ሕጉም ኧረ ጌቶቼ ባለፈው ታምራት ላይኔ በሥዬ ላይ የምስክርነት ቃሉን ይሰጠናልና ጊዜ ይሰጠን ብዬ ጠይቄ ፍ/ቤቱ አጭር ቀን ነው የሰጠን። አሁን ደግሞ ታምራት ላይኔ የገባውን ቃል ለውጦ ምንም ዐይነት የምስክርነት ቃል እንደማይሰጠን ነገረን። እናም አሁን ችግር ውስጥ ገብተናል። ዛሬ እናንተ እንደትዕዛዛችሁ ከፈጸማችሁ ወንጀለኛ ሊያመልጥ ነውና ቢያንስ የአንድ ወር ጊዜ ፍ/ቤቱ ቢተባበረን ብዬ ነው በሚል አነጋገር ቀረበን። ሰብሳቢው ከዚህ በኋላ በል እንወያይበት ውጣ አለው። ከዚያም ፍሰሐ ምን ትላላችሁ? ይለናል። ይህን ጊዜ ዳኜ ፈጠን ብሎ እጁን ያወጣና ነገሩን እኔም አሁን ሳየው ትንሽ የቸኮልን ይመስለኛል። ሙስና በመሠረተ አነሳሱ ሲታይ እጅግ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚፈጸም መሆኑን እናውቃለን። ስለዚህ አንድ ረዘም ያለ ቀጠሮ ልንሰጥ ይገበናል ብሎ ቁጭ አለ።

ከላይ እንዳልሁት፣ ከእኔ ቀጥሎ ወደ መንበረ ቢሮ ሲገባ አይቻለሁ። አነጋገሩም ከመንበረ የቀረበለትን የምልጃ ቃል ተቀብሎ መውጣቱን ያመለክታል። ዳኛ በሕግ ሳይሆን በአስተዳደሩ እየተመራ መሄድ ከጀመረ፣ የዳኛም፣ የፍርድ ቤትም መኖር አስፈላጊ አይሆንም። ፍርዱም የዘፈቀደ ፍርድ ይሆናል። እናም ነገሮች ፈራቸውን ለቀው፣ ወደ አዘቅት መግባታቸው ታየኝ። የእጁ አወጣጥና አነጋገሬም የንዴት መሆኑ እስከ አሁን ድረስ ትዝ ይለኛል። እንዴት ነው ነገሩ? በዘፈቀደ ነው እንደ እስከዛሬ ድረስ ስንወስን የነበርነው? አለቆቻችን ለማስደሰት ነው እንደ እየወስንን የነበርነው? ቀደም ብለን ዛሬ የመጨረሻው አድርገን ትዕዛዝ የሰጠነው አውጥተን፣ አውርደን ከሕጉ ጋር አዛምደን ነው። ያንን ሽረን ሌላ ትዕዛዝ ለመስጠት መሞከር፣ ይግባኝ እንደማየት ያህል ነው። እናም እኔ በበኩሌ የሰጠሁትን ቃሌን የምለውጥበት ምክንያት የለምና በአሳቡ አልስማም አልሁ። ግራ የገባው ሰብሳቢያችን በሉ ተወያዩ አለ እንደገና። እኔ ትዕግሥት አጣሁ መሰለኝ ሳላስፈቅድ ገባ ብዬ ኧረ አቶ ፍሰሐ ባልሆነ ነገር ላይ ለምንድነው የምታወያየን? ስል፣ ዳኜም የገባው ቃል ጨንቆት መሰለኝ ምንድነው የኛ ቃል የእግዚአብሄር ቃል ነው? ለምን አንወያይም ብሎ ብድግ አለ። ይህንኑ በትዝብት ያይ የነበረው ቆፍጣናው ጌታቸው ምህረቱ ብድግ አለና ወልዴ ልክ ነው። እንዴት አድርገን ነው ትናንት የሰጠነውን ትዕዛዝ ዛሬ የምንሽረው? ይህማ የዳኝነት ተግባር አይደለም። እኔም አልስማም አለ በቁጣ ቃል። በዚህ ላይ ሌሎችም አቋም ያዙ። ተዶልቶ የነበረው ቅመራ በዚህ ዓይነት ከሽፈና የቀድሞ ትዕዛዛችን ጠብቀን ለመሥራት ወጣንና ፈጸምነው። ከዚህ በኋላም መንበረ እንደአባት ገዳይ ያሳድደኝ ጀመር። ወደ መጀመሪያ ደረጃ ም/ፕሬዚዳንት የወረድሁትም አስተዳደርን ፈልጌው ሳይሆን፣ ከመንበረ ገለል ያልሁ መስሎኝ ነው።

በነገራችን ላይ ከጥቂት ወራት በፊት ጌታቸው ምህረቱና ሆሳዕና የተባለች ዳኛ ከጠቅላይ ፍ/ቤቱ መቀነሳቸውን ሰማሁ። በጣም ጠንካራ ዳኞች ነበሩ። ካመኑበት የሚነቀንቃቸው ምንም ሃይል የሌላቸው ዳኞች ነበሩ። ከከፍተኛ ፍ/ቤትም እነደዚሁ የተቀነሱ እንዳሉ ሰማሁ። አዘንኩም። የዳኝነት ነጻነት በሌለበት አገር፣ እንዴትስ ዳኛና ዳኝነት ይጠበቃል? የጋምቤላ ጉዳይ ጸሐፊ የነበረው ተገኔ ጌታነህ የአቶ ከማል ቦታ ተረክቦ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መሆኑንም ሰማሁ። አይ የወያኔ ሥራ አልሁ። ሥራውን ሁሉ የሚሰራው፣ የሚያዘው ምክትሉ መንበረፀሐይ ነው። ተገኔ የጋምቤላው ጉዳይ እንደውለታ ሆኖለት ለፖለቲካ መጠቀሚያ ነው እንዲቀመጥ የተደረገው ለማለት ይቻላል። ነገርን ነገር ያነሰዋል ዓይነት ሆነና ነው አልፎ፣ አልፎ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ስል ወደ ሌላ ጥልቅ የምለው።

ውድ አንባቢያን ከፍ ሲል ለሥዬ ጉዳይ መንበረፀሐይ ሰብሳቢ እንደሆነ በሕመም ሰበብ ከፍ/ቤቱ ጠፍቶ እንደነበረ ገልጬአለሁ። ምክንያቱ ምን ነበረ? እንደ ግንቦት 82 የደርግ ከፍተኛ የሠራዊቱ አባላት ዓይነት ከሸፈባቸው እንጂ ሥዬና ጓደኞቹ በመለስና አስተዳደሩ ላይ ያደረጉት እንቅስቃሴ የኩዴታ ዓይነት እንደነበር ነው ከእኔ ጋር በወቅቱ ይሰሩ ከነበሩት የስቢል ሰርቢስ ምሩቃን የሆኑት ዳኞች ያረጋገጡልኝ። እነ ሥዬ ታዲያ በወቅቱ ያዘጋጁት ከሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሲቢል ባለሥልጣናትም ነበሩባቸው። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በመለስ ተፈልጎ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ፕሬዚዳንት የበቃው ይኸው መንበረፀሐይ ታደሰ ነው። ይህንኑ ያረጋገጥሁት አሁን ሞቶአል ነፍሱን ይማረውና የቀድሞው አስተማሪዬ በኋላ የጊዜ ነገር ሆነና አብረን በጠቅላይ ፍ/ቤት በዳኝነት አንድ ላይ እንሰራ ከነበረው ከመስፍን ገ/ሕይወት ነው። ከፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሹመት ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደገባሁ፣ በወንጀል ችሎት የተመደብሁት ከመስፍን ጋር ነበር። መስፍን ጋር በጣሙን እየተግባባን መጣን። ምንም እንኳ በዘሩ ትግሬ ቢሆንም፣ የወያኔ አካሄድ ደስ እንደላለው ሁሌ ስንገናኝ በጨዋታ ላይ ይነግረኛል። አንድ ቀን በጫወታ መሃል ኧረ መንበረ ጠፋ እኮ። ምንድነው ነገሩ አልሁት። እባክህን ሰው የሚለውን አይሰማም። በየቦታው ጥልቅ እያለ አሁን ችግር ውስጥ ገብቶ መሸሸጉ ነው እንጂ አልጠፋም፤ እቤቱ ነው ያለው አለኝ። ከምንድነው የሚሸሸገው? ብዬ ጠየቅሁት ለማጣራት ስል። ከሥዬ ጋር አብሮ ነዋ ብሎኝ አፌን አስያዘኝ። ኧረ ጉድ ነው በሆዴ አልሁ። እናም መንበረ በሥዬ ጉዳይ ከሰብሳቢነቱ የራቀበት ምክንያትም ገባኝ። መስፍን የስኳር በሽተኛ ሆነ። መጨረሻው ላይ ያለእኔ ጓደኛ አልነበረውም ማለት ይቻላል። ጧት ሁልጊዜ እጽ/ቤቴ ይመጣና እባክህን ቁርሴን አልበላሁም ይለኝና ተያይዘን ወደ አምስት ኪሎ ሻይ ቤቶች እንሄዳለን። አንድ ኬክና

ቡና ያዛል። ግን ያችን የአንድ ጉርሻ ኬክ ሳያጋምሳት በቃኝ ይላል። በመጨረሻም በሽታው እየጸናበት መጥቶ ከዚህ ዓለም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሸለበ።

ታዲያም ሥዬ እኔ የሰራሁት ኮራፕሽኝ የለም። ማስረጃም አያገኙብኝም እንዳለውም እኛ የጊዜ ቀጠሮውን እንዲቋረጥ አድርገን ክሱን የጸረ-ሙስና ዐቃቤ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እስከሰጠን ድረስ ማስረጃ እንዳላገኙበት ነው። በኋላም እንደሰማሁት ለማግኘት እንዳልቻሉ ነው። መንበረ ይቅርታ እንደ ዐባይ ፀሐይ ጠይቆ ነው መሰለኝ፣ ወደ ፍ/ቤት እንደተመለሰ ነው እኛን የጊዜ ቀጠሮውን እንድናራዝም ምልጃውን የጀመረው። እኔ ወደ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሄድሁበት አካባቢ ጀምሮ ሰብሳቢነቱ በሥዬ ላይ ጀመረ። በኋላም መለስን ለመካስ ነው መሰለኝ ዳኞች አልተሟሉም የሚል ሰበብ እየፈጠረ ያለ ማስረጃ ለስድስት ዓመታት ያህል በእሥር ሥዬ እንዲማቅቅ አደረገው።

እንግዲህ በትንሹ ጀምሬ ስለሥዬ ያየሁትና የሰማሁትን ዘረገፍሁ። ይህን ሳደርግ ከሥዬ ጋር ዝምድና ወይም እውቅና ኖሮኝ አይደለም። ፊትለፊት ያየሁት በፍርድ ቤት ነው። የተነሳሰሁትና የገለጽሁት ከእውነት ተነስቼ ከእውነት ጋር ለማያያዝ እንጂ። በፖለቲካም ሆነ በጦርነት ጊዜ ጠላትን ማሸነፍ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ የጠላትን ጎራ ማፍረስ፣ የራስን ጎራ መገንባት ነው። እንዲህ ሊሆን የምችለውም ከጠላት ወገን የሚወጡትን ወይም የሚመጡትን እንደየሁኔታው አሸም ብሎ በመቀበል ነው። ሥራውንም ማየትና መከታተል ነው። ይህ ሳይሆን ትናንት እንዲህ ኖረህ፣ እንዲህ አድርገህ እያልን ቁስልን እየነካኩ ማበረር ለዛሬው የሚበጅ አይሆንም። ለማናቸውም ጊዜ አለውና። እንዲህ ዓይነት አካሄድ ብስለት የሚታይበት የሰለጠነ ፖለቲካ አካሄድ አይመስለኝም። የዛሬውን ተከታትሎ ማየት ብልህነት መሰለኝ። ትናንት እንደዚያ የነበረ ዛሬ እንደዚህ አይሆንም ብሎ ማለት በሰው ልጆች ውስጥ ለውጥ ሊኖር አይችልም እንደማለት ነው። እንዲህ ከሆነም፣ ማንዴላን የምናደንቀው ምንም ሳይገባን ነው ማለት ነው? ኧረ አስትውሎቱ ይኑረን። ከፈረሱ ጋሪውን ማስቀደሙ ይቅርብን። ለነገሩ በአገር ቤት ያለው ሕዝብ ሥዬም ሆነ ዶ/ር ነጋሶ ከህብረ ብሔር ፓርቲዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲሰሩ በየጊዜው ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ታዲያም ግራና ቀኙን አይተውና አመዛዝነው ሲመጡ ማየት ሲኖርብን ከአሁኑ ምን አይተው ነው በሚል ግምት ብቻ ለማባረር መሞከር ሎጅካዊም አይደለም። ደግሞም የፓርቲ መሪዎችና አባላትን ምንም አያቁም፤ እኛ ብቻ ነን አዋቂዎች አንበል። ቢያንስ ፍርድ ከመስጠታችን በፊት እነርሱ ቦታ ራሳችንን እናስቀምጥ። እንዲህ ካላደረግን ፍርዳችን ስሜታዊ ይሆናል።

እናም ወገኖቼ ትናንት ዛሬ ላይሆን ተሰናብቶን አልፎአል። ዛሬ ሌላ ነው። ዛሬ ሌላ ዓለም ነው። ዛሬ ሌላ አሳብ ነው። ዛሬ ላለፈው ክረምት ቤት መሥራት ፍጹም እንዳይቻል የሆነበት ነው። በትናንቱ ላይ ብቻ ተሰቅለን የዛሬውን ሳናይ ወደ ፍርድ ብንሄድ፣ ፍርዳችን ፍርደ-ገምድል ይሆናል። ነገር እናበላሻለን። ቀደም ስል እንደጠቃቀስሁት፣ ትናንት ከልደቱ ወዲያ ደፋርና ታጋይ ብለን የዚያ የደጉንና አስተዋዩን ሰው የማንዴላን ስም ሰጥተነው ነው ነበር። እርሱ ግን ባለበት ሳይጸና በምርጫ 97 ማግሥት እንደሸጠን አየን። ትናንት ከሰሎሞን ተካልኝ ወዲያ ታጋይ ሙዚቀኛ ላሳር ብለን ነበር። ዛሬ ሰሎሞን የአርበኞችን ግንባር ምስጢር ለወያኔ ካሳ ሸጦ የት እንዳለ አየን። ትናንት መምህራኑ፣ ተማሪው፣ ጋዜጠኛው፣ ኧረ ስንቱ፣ እንዲያው በጠቅላላው ሕዝባችን ማለት ይቻላል የተዋደቀለት ሰው ዶ/ር ታዬ ዛሬ ምን እንደሰራ፣ የት እንዳለ አይተናል። ትናንት ደግሞ አንበሳ ተብለው የተሞገሱትና ያለ እርሳቸው በቀር ማን አለ ተብለው እንደዚያ ሲወደሱ የነበሩት እንጅነር ኃይሉ ሻውል፣ ቅንጅትን አፍርሰው፣ በወያኔ ተረቆ የምርጫ የሥነ- ምግባር ደንብ በሚል በቀረበው የሃሞራባዊ ሕግ ላይ ፈርመው፣ ከዚህ ወዲያ ዲሞክራሲ ከየት ይምጣ! ልዩ ሕገ-መንግሥት፣ ሊያሰራን የሚችል እያለን ሲሉና ሲደሰኩሩ ሰማን የነዚያ ለዲሞክራሲ ሲሉ የተሰው ወጣቶች፣ ጎልማሶች፣ አዛውንቶችና እምቡጥ የነገውን ኢትዮጵያናችን ተረካቢዎች የተሰውበትን ረስተው፣ ሁሉን ወደ አዲዮስ ወርውረውት። እንደዚያ በአገር ቤትና በውጭ ያለው ማህበረሰባችን ተሟሙቶ ለዚህ ከበቃው ተወዳጁ ድምጻዊ ከጧቱ እንግዲህ እጅህ ከምን? ልንለው ከጅለን ነበር የትናንቱን ሥራውን እያሰብን። ግን ቴዲ ያች በሕዝብ ልብ ውስጥ፣ በታጋዩ ውስጥ ገብታ እደግ ተመንደግ ያስኘውን ሙዚቃ እንኳ በፍትለፊት ሊያስደምጠን ሲሳነው ሰማን። አንድ ወቅት እንዲያ የነበረ ሰው ፈጣሪ፣ ፈጣሪ ማለቱ ባይከፋም፣ ካበዛው ነገር አለው ያሰኘኛል። ብቻ እንጃ ከአንድያችንና ጀግና ከሻምበል ጋር ብቻ ልንቀር ይሆን? ይህንኑ ዛሬውኑ ልናይ ነው። እዕድሜ ከሰጠን ደግሞ ነገ ሌላ እናይ ይሆናል። በበኩሌ ይኸ ሁሉ ያሳዝነኝ እንጅ አያስገርመኝም። ምክንያቱም ያለና የሚኖርም ስለሆነ። የሰው ማንነት በትናንት ብቻ ግን አይለካም፣ አይደመደምም ውድ ወገኖቼ።

ምናልባትም አንዳንዶቻችን ምክንያት አጥተን ነው መሰለኝ፣ ይቅርታ ሥዬ መቼ ጠየቀ ለሰራው ግፍ እንላለን። ለነገሩ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፣ ከእስር ሥዬ እንደወጣ በቪ..ኦ.ኤ ላይ ቀርቦ አሁን ወደ ኋላ ስለፈጸሙት ድርጊት ምን ይሰማዎታል? ተብሎ ሲጠየቅ፣ ወጣትነት መጥፎ ነው። በወጣትነት ክፉና ደጉን መለየት አስቸጋሪ ነው። እኛ የሰራናቸው ትክክል ነው ብለን ነበር። ዕድሜ ሲጨምር ብዙ ትማራለህ፣ እየተማርሁ መጣሁ። በተለይም በእስር ቤት ብዙ ተምሬአለሁ። አሁን የድሮው ሥዬ አይደለሁም። ለሕዝቡ ጥሩ ነገር ለመሥራት ራሴን ለመለወጥ ተዘጋጅቻለሁ ነበር ያለው። ይህ አነጋገር በእኔ አተረጓጎም ከአሳማኝ ምክንያት ጋር ይቅርታ ማለት ይመስለኛል። እርግጥ ነው ወጣትነት ቸኩልነት፣ ግንፍልነት፣ እንደመሩት መመራት፣ የአስተውሎት ጉድለት፣ እና የመሳሰሉት የሚታይበት እድሜ ለመሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው። እናም አነጋገሩ እውነትነት ያለው ነው። ሥዬ በአገር ቤት በየስብሰባዎች እየተገኘ የሚያቀርባቸው ጽሑፎች፣ የሚናገራቸው ነጥቦች ሁሉ፣ በተለይም በድርጎ ለሱዳን በመለስ የተሰጠውን የጎንደርን መሬት በተመለከተ ሌላ ማንም ሳይኖር በድፍረት ወጥቶ የምስክርነት ቃል መስጠቱን ስሰማና ሳስተውል፣ ለእኔ ከሺህ ጊዜ ይቅርታ አንድ ተግባር ያሰኘኛል። ቃል አንድ ነገር ሆኖ ለእኔ ከቃል ይበልጥ ተግባር ይበልጥብኛል። ስገምተው ሥዬ የተግባር ሰው ይመስለኛል። ምናልባት ሥዬ ወደ አንድነት መቀላቀሉ ለብርቱካን

ጉዳይ እንደማለፍያም ይታየኛል። ለነገሩስ መጀመሪይውኑ ከነሥዬና ከመድረክ ጋር ለመሥራት የብርቱካን ጥንስስ አለበት አይደል? ዶ/ር ነጋሶም ቢሆኑ፣ በዚያ በኢህአዴግ ስብሰባ ላይ ተነስተው መለስን አሁንስ መንግሥቱን መሰሉኝ ብለው መድረኩን ረግጠው ከወጡ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያንን ሁሉ ረስቶ በወቅቱ ወንድ! ብሏቸዋል። ከዚያም ወደ ሕብረብሔር ፓርቲዎች እንደሥዬ እንዲቀላቀሉ ሲጎተጉታቸው እንደነበር በአገር ቤት ሳለሁ አውቃለሁ። እንዲያውም አሁን ሁለቱ በዚህ አጉል ጊዜ ወደ አንድነት መቀላቀላቸው እሰዮ የሚያሰኝ እንጅ የሚያስከፋ አይሆንም። ሥራቸውንና የሚያበረክቱትን ፋይዳ ደግሞ መከታተል ግን ያለ እውነታ ነው።

ውድ ኢትዮጵያን ወያኔ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ሥልጣን ይለቃል የሚል ሕልም አይደለም እንኳ ቅዠትም አይነካካኝም። ይሁንና አንድ ድንጋይ በጠላት ላይ መወርወር ቀላል አይደለም። የጠላትን ጎራ እያፈርሱ የራስን ወገን መገንባት ብልህነት እንጅ ጅልነት ከቶውንም ሊሆን አይችልም። ወያኔ ለሥልጣን እንዴት እንደበቃ መለስ ብለን ማስተዋሉ ግንዛቤ ያስጨብጠናል። ከኢህፓ የተገነጠሉትን በቀድሞው ኢዲን፣ በአሁኑ ብአዲንን ይዞ፣ ከቀድሞ ጦር እጅ እየሰጡ የሚገቡትን ወታደሮችን አሸም ብሎ በመልካም ተቀብሎ አሰልፎ እንጅ በራሱ ኃይል ብቻ አይደለም። እኛስ በዚህ መልኩ ለምን አንጠቀምም? ትግል፣ ፖለቲካ ብስለት የተሞላበት ብልሃትንና አስተውሎትን የሚጠይቅ ነው። በትናንት መዝፈንን አውልቆ መጣልን ይጠይቃል። እናም ወገን፣ ነገረ-አነሳሴ እንዲህ ወጣ-ገባ ማለቴ ለሌላም አይደለም። ከጠላት ወገን እየፈለሱ የሚመጡትንና በተግባር የበደሉትን ማህበረሰብ ለመካስ የተዘጋጁትን ከዛሬው እውነታ ጋር በማይሄድ መልኩ ባናንብጠለጥል፣ እንሞክራለን ብለው በአገር ቤት በተለይም ከአንጀታቸው በተቻላቸው መጠን በእኔ ግምት ይለፋሉ የምላቸው እንደ አንድነትና መድረክ ያሉት ላይ የምንሰጠው ትችት፣ ራሳችንን በነርሱ ቦታ ባስቀመጠ መልኩ ይሁን፣ እኛ ገንዘብ ብቻ ስለምንረዳቸው፣ እነርሱን ዝቅ አድርገንም ባንመለከታቸው ለማለት ነው። እንዲህ ሳናደርግ የምንሰጠው ትችት የዘፈቀደ ይሆንና ከገንቢነቱ ወደ አፍራሽነት እንዳይዘልቅም ጥንቃቄ ያስፈልጋል ለማለት ነው። እኛ ብቻ አዋቂ፣ እኛ ብቻ አሳቢም ራሳችንን አናድርግ ለማለት ነው። እንግዲህ ወደዚህ ከደረስን እላይ ያስቀምጥኳቸውን ጥያቄዎቼን መለሳችሁ ማለት ነው።

እናም፣ ኣረ እየተስተዋለ ይሁን ሁለ-ነገራችን!